ቁጥር/ Ref.No. 7/0171/15
ቀን/Date ሐምሌ 2 5 2015

በአባሪ ለተጠቀሱ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
በያሉበት

ጉዳዩ፡- በታሪፍ መጽሐፍ ነጻ የተደረጉ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችን ይመለከታል፡-

ከገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማአ30/7/214 ግንቦት 18 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የሚመደቡበትን የታሪፍ ቁጥር በመጥቀስ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ ሀገር እንዲገቡ በተፈቀደው መሰረት በ2017 ታሪፍ መጽሐፍ ላይ ነፃ እንዲሆን የተደረጉ መሆኑን ተከትሎ መሳሪያዎቹ ለታለመላቸው ዓላማ ብቻ መዋላቸውን በጉምሩክ ኮሚሽን የክትትልና ቁጥጥር ስራ መሰራት አለበት ወይስ የለበትም የሚለው አሻሚነት የነበረው በመሆኑ ለሚኒስቴሩ በቀን ሃምሌ 19/2014 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 7/0010/15 ማብራሪያ እንዲጠየቅ ተደርል፡፡

በዚሁ መሰረት ሚኒስቴሩ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ተሰጠ የሚባለው ከጅምሩ ዕቃዎቹ በታሪፍ መጽሃፉ መሰረት ቀረጥና ታክስ የሚጣልባቸው ሆነው መንግስት ለተለያዩ አላማዎች ሲባል ይህንኑ ቀረጥና ታክስ ለተፈቀደላቸው ሰዎች ብቻ ቀሪ ሲያደርግ መሆኑን እና በዚህ መልኩ ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች መብቱ ሲፈቀድ ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን በመጥቀስ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ግን በ2017 ታሪፍ መፅሃፉ ነፃ የተደረጉ በመሆኑ እንደ ቀረጥና ታክስ ነፃ ልዩ መብት ሊቆጠሩ አይገባም፣ ክልከላ፣ ቁጥጥር እና ሌሎች እርምጃዎች እንዲወሰዱ አይጠበቅም በማለት ሌሎች ጉዳዮችንም በማካተት በቁጥር ማአ30/7/9400 በቀን 07/03/2015 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ በመሆኑም ለአፈፃፀም ይረዳችሁ ዘንድ የተላከልንን 3 ገጽ ማብራሪያ በዚህ ሽኚ ደብዳቤ አያይዘን ልከናል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ተገኔ ደረሰ ደገፉ
የህግ ተገዥነት ዘርፍ ተወካይ

ግልባጭ//
- ለክቡር ኮሚሽነር
- ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለበመ/የተ/የቀ/ነፃ/መ/ክ/ቁ የስራ ሂደት

ጉምሩክ ኮሚሽን

<u>አባሪ፡-</u>

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬድዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሐዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሰመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>

Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1

ህ07/1074 ... 12/10ቀ/15 - ዐ1/12/22.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የገንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

**MINISTRY OF FINANCE**

ቁጥር / Ref.No ማኢ30/7/9400

ቀን / Date 7/3/2015

ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጉምሩክ ኮሚሽን

አዲስ አበባ

ጉዳዩ: <u>በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ማብራሪያ መስጠትን ይመለከታል</u>

የጉመሩክ ኮሚሽን ጳጉሜ 1 ቀን 2014 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 6/0185/15 እና ሐምሌ 19 ቀን 2014 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 7/0010/15 በተጻፉ ደብዳቤዎች መሰረት ከገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ.30/07/214 ግንቦት 18 ቀን 2013 ዓ.ም በተላለፈ ዉሳኔ መሰረት የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች እንዲሁም በ2017 የታሪፍ መጽሐፍ እነዚሁ እቃዎች ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ እንዲሆኑ መደረጋቸዉን ተከትሎ የጉሙሩክ ኮሚሽን በአፈጻጸሙ ላይ ለተነሱ የሚከተሉት ነጥቦች ላይ ማብራሪያ እንዲሰጠዉ ጠይቋል::

1) በታሪፍ ቁጥራቸዉ ነጻ ሆነዉ የገቡ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ለታለመላቸዉ አላማ ብቻ መዋላቸዉን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ የሚጠበቅበት ወይም የማይጠበቅበት ስለመሆኑ፣
2) ዕቃዎቹ በታሪፍ መጽሃፉ ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ከመደረጋቸዉ በፊት በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች በተናጠል ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ወደ ሃገር የገቡት እቃዎችን በተመለከተ፤
   - 2.1 የብድር ማስያዣነት ጥያቄ ሲቀርብባቸዉ የሚስተናገዱበት አግባብ፣
   - 2.2 እቃዎቹ ላይ የመድህን ሽፋን ከተገባላቸዉ በኋላ በታሪፍ መጽሃፍ ከጉሙሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ የተደረጉ ሲሆን ጉዳት ከደረሰባቸዉ በኋላ የሚከፈለዉ የመድህን ካሳ ላይ ቀረጥ እና ታክስ መከፍል ያለበት ስለመሆኑ/አለመሆኑ እና
   - 2.3 የተሰጣቸዉን የቀረጥ እና ታክስ ነጻ መብት አላግባብ በመጠቀም ተይዘዉ በክርክር ሂደት ላይ ያሉ የካፒታል እቃዎች እና ተሽከርካሪዎች በምን መልኩ መስተናገድ እንዳለባቸዉ ጠይቋል::

በጉሙሩክ አዋጅ (እንደተሻሻለ) ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 129 እና 130 መሰረት የቀረጥ እና ታክስ ነጻ መንግስት ለተለያዩ አላማዎች ሲባል በታሪፍ መጽሃፉ መሰረት ቀረጥ እና ታክስ የሚከፈልባቸዉን እቃዎች በልዩ ሁኔታ ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ እንዲሆኑ የሚሰጠው መብት ነዉ:: የቀረጥ እና ታክስ ነጻ መብት ተሰጠ የሚባለዉ ከጅምሩ እቃዎቹ በታሪፍ መጽሃፉ መሰረት ቀረጥ እና ታክስ የሚጣልባቸዉ ሆነዉ መንግስት ለተለያዩ አላማዎች ሲባል ይህንኑ ቀረጥ እና ታክስ ለተፈቀደላቸው ሰዎች ብቻ ቀሪ ሲያደርገዉ ነዉ::

ስልክ 251-11-155 24 00, 22 66 98 251-11-155 00 81. 83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.BOX 1905,1037
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet

Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የገንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

**MINISTRY OF FINANCE**

ቁጥር ______________
Ref.No
ቀን ______________
Date

በዚህ መልኩ ወደ ሃገር የገቡ እቃዎች መብቱ ሲፈቀድ ለታለመላቸዉ አላማ መዋላቸዉን ለማረጋገጥ ጥብቅ ቁጥጥር ይደረጋል። ለአብነትም ተመሳሳይ የጉሙሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ መብት ለሌለዉ ማንኛዉም ሰዉ መተላለፍ አይችሉም፣ ከተሰጠበት አላማ ዉጭ መገልገል፣ እና በሌሎች ሰዎች ይዞታ ስር ማድረግ እንዲሁ ክልክል ነዉ። በተጨማሪም ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ መብትን በመጠቀም የገቡት እቃዎች ለብድር ዋስትናነት የሚሰጡበት አግባብ እና ወደ ሃገር ከገቡ በኋላ እቃዎቹ ላይ ለሚደርስ የጉዳት ኢንሹራንስ ክፍያ በሚመለከትም ቁጥጥር ይደረጋል።

የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ30/07/2014 ግንቦት 18 ቀን 2013 ዓ.ም በተላለፈ ዉሳኔ መሰረት በ2017 የታሪፍ መጽሐፍ ላይ ማሽነሪዎችን ጨምሮ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን የእነዚህ ዉሳኔዎች ዉጤት የኮንስትራክሽን እቃዎቹን ከቀረጥ እና ታክስ በታሪፍ መጽሃፉ ላይ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ማንኛዉም አካል ሲያመጣቸዉ በእዚሁ አግባብ እንዲስተናገዱ ነዉ። ከላይ እንደተመለከተዉ በታሪፍ መጽሃፉ መሰረት ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የተደረጉት የኮንስትራክሽን እቃዎች እንደ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ ልዩ መብት ሊቆጠሩ አይገባም፡ ፡ በዚህም መሰረት ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ መብትን የተመለከተው ክልከላ፣ ቁጥጥር እና ሌሎች እርምጃዎች እንዲወሰዱ አይጠበቅም።

የቀረጥ እና ታክስ ነጻ መብትን በመጠቀም ወደ ሃገር የገቡ እቃዎች ሲተላለፉ መከፈል ያለበት ታክስ እና ቀረጥ በአዋጁ አንቀጽ 130 (2) መሰረት ሊሰላ የሚገባዉ እቃዉ በተላለፈበት ጊዜ በሚያወጣዉ ዋጋ እና ጸንቶ ባለዉ የታሪፍ ልክ መሰረት ነዉ።

እንዲሁም ከቀረጥ ነጻ በገባ ዕቃ ያለአግባብ የተገለገለ ሰዉ በአዋጁ አንቀጽ 163(1) መሰረት እቃዉ በተያዘበት ጊዜ ወደ አገር እንደገባ ተቆጥሮ ለዕቃዉ ሊከፈል የሚገባዉ ቀረጥ እና ታክስ መከፈል ያለበት ሲሆን በዚሁ ላይ የቀረጥ እና ታክሱ ሃምሳ በመቶ እንዲጨመር ይደረጋል። በሌላ በኩል ጉሙሩክ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀጽ 2(46) መሰረት ከጉሙሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ የገቡ እቃዎችን ተመሳሳይ መብት ለሌለዉ ሶስተኛ ወገን ያስተላለፈ እንደሆነ፣ መብቱ ከተሰጠበት አላማ ዉጭ አገልግሎት ላይ ያዋለ እንደሆነ እና ለኢንቨስትመንት ከተፈቀደዉ ቦታ ዉጭ ለሽያጭ አከማችቶ የተገኘ እንደሆነ መንግስት እቃዉን ከመዉረሱ በተጨማሪ የገንዘብ መቀጮ እና የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል።

ስልክ 251-11-155 24 00, 22 66 98 251-11-155 00 81, 83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.BOX 1905,1037
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
MoF Ethiopia facebook.com/MoFEDet

ቁጥር ____________
Ref.No
ቀን ____________
Date

ከላይ በተገለጸው መሰረት፤

1. የኮንስትራክሽን እቃዎች እና ማሽነሪዎች በታሪፍ መጽሃፉ መሰረት ነጻ እንዲደረጉ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ወደ ሃገር የገቡ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች እና ማሽነሪዎች ላይ ለገቡበት አላማ ስለመዋላቸው የሚደረገው ቁጥጥር እና ክትትል ተፈጻሚ አይደረግባቸውም፣
2. ዕቃዎቹ በታሪፍ መጽሃፉ ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ከመደረጋቸው በፊት ወደ ሃገር የገቡ ከሆነ እና አሁን ላይ የብድር ማስያዣነት ጥያቄ ከቀረበባቸው የአዋጁ አንቀጽ 130(6) ገደብ ተግባራዊ አይደረግባቸውም፣
3. በታሪፍ መጽሃፉ ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ከመደረጋቸው በፊት ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ መብትን በመጠቀም ወደ ሃገር የገቡት እቃዎች የመድህን ሽፋን ከተገባላቸው እና ጉዳት ሲያስተናግዱ የሚከፈለው የመድህን ካሳ ላይ ቀረጥ እና ታክስ ለመክፈል የሚቀርበው ጥያቄን በተመለከተ ሊስተናገዱ የሚገባው ለዕቃው የመድህን ዋስትናበሚከፈለው ጊዜ በሚያወጣው ጸንቶ ባለው የታሪፍ ልክ መሰረት ስለሆነ በዚሁ አግባብ መስተናገድ አለባቸው፣ እና
4. የተሰጣቸውን የቀረጥ እና ታክስ ነጻ መብት አላግባብ በመጠቀም ተይዘው በክርክር ሂደት ላይ ያሉ የካፒታል እቃዎች እና ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ማሻሻያው ከመደረጉ በፊት ጸንቶ በነበረው ህግ እና አሰራር መሰረት መስተናግድ አለባቸው፡፡ ማሻሻያው ከተደረገበት ቀን በኋላ የተጀመሩ ጉዳዮች እና ክርክሮች ሊስተናገዱ የሚገባው ከመሰረቱ ቀረጥ እና ታክስ እንደማይከፈልባቸው እቃዎች ሆኖ በእዚሁ አግባብ ጉዳዮቹ እልባት እንዲያገኙ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

...ብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፡-

- ታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
  ገንዘብ ሚኒስቴር